Montgomery County Public Schools
UNLEASHING POTENTIAL

2025-2026
የተሻሻለ

# ስለ ጾታ መለያ/ማንነት

## በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ

## ዕሴት፡-

ትምህርት
መከባበር
መልካም ግንኙነት
ልህቀት/ምጡቅነት
ፍትኃዊነት

## ራእይ፡-

የወደፊት ዝግጁነት፡-
በተለዋዋጭ አለም ውስጥ ሁሉም ተማሪዎች ለእድገት፣ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ለመድረስ፣ እና ለስኬታማነት ዝግጁ ሆነው ይመረቃሉ— በማህበረሰባቸው ውስጥ እና ከዚያም በላይ ለመሪነት፣ ለአገልግሎት፣ እና በጎ ተጽእኖ ለመፍጠር በሚያስችላቸው እውቀት፣ ችሎታ፣ እና በራስ በመተማመን ተገንብተው ይመረቃሉ።

## ተልእኮ፡-

እምቅ አቅምን በተግባር እንዲገለጥ ማድረግ፥
ሁሉም ተማሪዎች ጥልቅ አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተ፣ ትምህርትን የማዳበር እና የማበልጸግ እድሎችን በመጠቀም ጠንካራ የአካዳሚክ መሠረት ይኖራቸዋል። ሁሉም ተማሪዎች ለውጦችን እና አዳዲስ ሁኔታዎችን መቋቋም የሚችሉ ሆነው ዕድሜ ልክ የመማር ፍላጎትና ጽናትን ያዳብራሉ። ሁሉም ተማሪዎች ትርጉም ባለው ግንኙነት ላይ የተመሠረተ መስተጋብር፤ ውጤት ላይ የሚያተኩሩ እና በትብብር የሚሠሩ ይሆናሉ። ሁሉም ተማሪዎች በማህበረሰባቸው ውስጥ አዎንታዊ ተጽእኖ ለመፍጠር የተዘጋጁ፤ እና በግል ህይወታቸው እና በሙያዊ ብቃታቸው ለስኬታማነት የሚተጉ ይሆናሉ።


**የትምህርት ቦርድ**
Board of Education

ሚ/ስ ግሬስ ሪቬራ-ኦቨን Ms. Grace Rivera-Oven
ፕሬዚደንት President

ሚ/ስ ብረንዳ ዎልፍ Ms. Brenda Wolff
ም/ፕሬዚደንት Vice President

ሚ/ስ ሪታ ሞንቶያ Ms. Rita Montoya

ሚ/ስ ካርላ ሲልቨስትሪ Ms. Karla Silvestre

ወ/ሮ ላውራ ስቲዋርት Mrs. Laura Stewart

ሚ/ስ ጁሊ ያንግ Ms. Julie Yang

ሚ/ስ ናታሊ ዚመርማን Ms. Natalie Zimmerman

ሚ/ስ አኑቫ ማሎ Ms. Anuva Maloo
ተማሪ አባል Student Member

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**
Montgomery County Public Schools

ቶማስ W. ቴይለር (ዶ/ር)
የት/ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት
Thomas W. Taylor, Ed.D., M.B.A.
Superintendent of Schools



15 West Gude Drive
Rockville, Maryland 20850
www.montgomeryschoolsmd.org

……………..

# ማውጫ


ፈጣን የማጣቀሻ መመሪያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . i

መግቢያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1

ትርጓሜ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1

ከትራንስጀንደር/የጾታ ለውጥ ያደረጉ እና ሥርዓተ-ፆታቸውን ይፋ ማድረግ ከማይፈልጉ ተማሪዎች ጋር በንቃት መስራት

የሥርዓተ -ፆታ ድጋፍ ዕቅድ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 2

ከቤተሰብ ጋር መግባባት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3

ግላዊነት እና መረጃን ይፋ ማድረግ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3

ስሞች/ተውላጠ ስሞች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3

የሰራተኞች ግንኙነት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3

ቋሚ የትምህርት ቤት ሪከርዶች. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 4

የአለባበስ ኮድ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 4

ጾታን መሠረት ያደረጉ እንቅስቃሴዎች/አክቲቪቲዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . 4

በጾታ የተለዩ ቦታዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 4

አዲስ ግንባታ/እድሳት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 5

የአካል ማጎልመሻ ትምህርት ክፍለጊዜዎች እና የት/ቤት ተማሪዎች ስፖርታዊ ውድድሮች. . . . . . . . . 5

በትምህርት ቤቶች መካከል የሚካሄድ አትሌቲክስ . . . . . . . . . . . . . . . . . . 5

ክለቦች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 5

ከቤት ውጭ ትምህርት/የሌሊት የመስክ ጉዞዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 5

የጉልበተኝነት፣ የትንኮሳ፣ ወይም የማስፈራራትና የዛቻ ምርመራ . . . . . . . . . . . . 6

ሠላማዊ ቦታዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 6

የሰራተኞች ድጋፍ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 7

# ለተማሪዎች ፈጣን የማጣቀሻ መመሪያ ግብአት

## በቀውስ ግዜ ክፍት የስልክ መስመር
24-ሰዓት መረጃ መስጠት፣ሪፈራል፣ እና በውይይት መርዳት

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ቀውስ ማዕከል**
Hotline/EveryMind/ . . . . . . . . . . . . . . 988
እና https://www.every-mind.org/
በይነመረብ ላይ የሚያነጋግሩ ሰዎች ያሉበት እና የድንገተኛ ጥሪ የስልክ መስመር፥ 24 ሰዓት የማወያየት አገልግሎት ይሰጣል።

Montgomery County Crisis Center . . . . . . 240-777-4000
**ሞንትጎመሪ ካውንቲ ቀውስ ማእከል**
ቀውስ ማዕከል የአእምሮ ጤና ችግር ላጋጠማቸው ግለሰቦች 24/7 ነፃ የድጋፍ አገልግሎት ይሰጣል።

Trevor Project . . . . . . . 866-488-7386፤ Text 678 678

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ወጣቶች ድንገተኛ የስልክ ጥሪ መስመር፡-**
Youth Crisis Hotline of Montgomery County . 988
በሰለጠኑ ካውንስለሮች አማካይነት 24 ሰዓት በስልክ የማማከር ድጋፍ እና ሪፈራል የምስጢር አገልግሎት ይሰጣል።

## የደህንነትና የፀጥታ አስጊ ሁኔታዎችን ሪፖርት ለማድረግ፡-

MCPS የደህንነት እና የድንገተኛ አደጋ ማኔጅመንት ክፍል 240-740-3066
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤቶችን እና ጽ/ቤቶችን ደህንነት የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለው ቢሮ።

MCPS Student Conduct and Appeals SWC@mcpsmd.org or SWC@mcpsmd.org . . . . . . . . . . . 240-740-3215
MCPS ዲስትሪክት አቀፍ Title IX አስተባባሪ እና ዲስትሪክት አቀፍ የሕፃናት በደል እና ቸልተኝነትን የሚመለከት ግንኙነት ሃላፊ። የተማሪ ስነምግባር እና ይግባኝ (SCA) ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል፡- www.montgomeryschoolsmd.org/compliance/ SCA ከትምህርት ቤቶች፣ ከህግ አገልግሎት ክፍል፣ እና ከሌሎች የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ቢሮዎች እና ከማህበረሰብ ኤጀንሲዎች ጋር በመተባበር የፖሊሲዎችን፣ የደንቦችን እና የመመሪያዎችን አፈፃፀም ወጥነት ለማረጋገጥ ከሰብአዊ የግንኙነቶች ክፍል ጋር በማቀናጀት ይሰራል። ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ (ታይትል IX ጾታዊ ትንኮሳ ጭምር) እና ማስፈራራት፤ የልጅ ጥቃትን እና ቸልተኝነትን ማወቅ እና ሪፖርት ማድረግ፣ ጥላቻ፣ አድሎአዊነት፣እና የተማሪ ጾታ ማንነት ክስተቶችን በሚመለከት አፈጻጸሙና ትግበራው ወጥነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ይሠራል።

MCPS Cyber Safety dropbox፡- . CyberSafety@mcpsmd.org
MCPS ውስጥ ተገቢ ያልሆነ ኦንላይን እንቅስቃሴን ሪፖርት ማድረጊያ Dropbox።

ከኮምፒተር ኔተዎርኮች ጋር ስለተገናኙ ጉዳዮች የጥቆማ መስመር - Cyber Tipline . . . . . . . . . . . . . . 1-800-843-5678
24/7 ልጆችን ለወሲብ ድርጊት በማባበል የተጠረጠሩትን ሪፖርት ለማድረግ የድንገተኛ ጥሪ የስልክ መስመር፣ ከቤተሰቦቻቸው ውጪ የሚፈፀሙ ወሲባዊ ድርጊቶች፣የህፃናት ፖርኖግራፊ፣የህፃናት ወሲባዊ ቱሪዝም፣የህፃናት የወሲብ ንግድ፣ለልጆች የሚላኩ ያልተጠየቁ ጸያፍ ቁሶች፣የተሳሳተ/የተጭበረበሩ የተጠቃሚ ስሞች እና አሳሳች ቃላትን ወይም በኢንተርኔት ላይ የሚለጠፉ ዲጂታል ምስሎችን ሪፖርት ለማድረግ 24/7 የሚያገለግል የስልክ መስመር።

Safe Schools Maryland Hotline 833-MD-B-Safe (833-632-7233)
ደህንነታቸው የተጠበቀ የሜሪላንድ ት/ቤቶች የአስቸኳይ ጊዜ ጥሪ መስመር 24/7 ስም ሳይገለጽ ነፃ የሪፖርት ማድረጊያ ስርዓት ለተማሪዎች፣ ለአስተማሪዎች፣ ለት/ቤት ሰራተኞች፣ ለወላጆች እና ለጠቅላላው ማህበረሰብ የአእምሮ ጤና ጉዳዮችን ጨምሮ ማንኛ ውንም የት/ቤት ወይም የተማሪ ደህንነት ስጋቶችን ሪፖርት ለማድረግ ያገለግላል። ስልክ የሚደውለውን ሰው ማንነት በመደበቅ ስለተፈጠረው ክስተት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ አግባብ ካላቸው ቢሮዎች ጋር መረጃ ይጋራል።

Montgomery County Child Protective Services, Department of Health and Human Services
**የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕፃናት ጥበቃ አገልግሎት፣ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት**
(24 ሠዓት ክፍት የስልክ መስመሮች)240-777-4417 ወይም 240-777-4815 TTY
ተጠርጣሪ የልጅ ጥቃትን ወይም ቸልተኝነትን ለሞንትጎመሪ ካውንቲ የልጆች ደህንነት ጥበቃ አገልግሎት ክፍል ለማሳወቅ 24/7 ሪፖርት የሚቀበል የስልክ መስመር።

**ለአደጋ ተጋላጭ ጎልማሶች የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጎልማሶች ጥበቃ አገልግሎት**
240-777-3000፤ 240-777-4815 TTY
በአዋቂዎች ላይ የሚጠረጠር ጥቃትን እና ቸልተኝነትን ሪፖርት ለማድረግ 24/7 ክፍት የሆነ የስልክ መስመር።

**የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፖሊስ መምርያ የልዩ ተጠቂዎች ምርመራ ክፍል (24 ሰዓት) ስልክ፡-** 240-773-5400
በልጆችና በጎልማሶች ላይ የሚፈጸሙ የወሲብ ወንጀሎችን፣ የአካል ጉዳተኛ ልጆችን፣ ሽሽተው፣ የጠፉ ልጆች፣ ከባድ የቤት ውስጥ ጥቃት፣ የተጋላጭ አረጋውያን ጥቃት/አደጋ በአዋቂዎች ላይ የሚደርስ በደል፣ እና የተመዘገበ ሪከርድ ያላቸው የወሲብ ጥቃት ወንጀለኞችን ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ መምሪያ ለማሳወቅ 24/7 የስልክ መስመር።

**የሞንጎሞሪ ካውንቲ ፖሊስ፡-**
**የአደንዛዥ ዕፅ እና የወሮበሎች**
(ጋንግ) የጥቆማ መስመር። . . . 240-773-GANG (4264) ወይም
240-773-DRUG (3784)
በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ህገ-ወጥ እጽ ማዘዋወር/የወሮበሎች ቡድን (ጋንግ) እንቅስቃሴዎችን የሚመለከት ማንነት ሳይገለጽ ጥቆማ ለማቅረብ 24/7 ክፍት የስልክ መስመር።

## MCPS ሪሶርሶች

**ካውንቲ አቀፍ የተማሪ አመራር**
www.montgomeryschoolsmd.org/departments/student-leadership

ዳይሬክተር፣ የተማሪ አመራር ተግባራት. . . . . . . 240-740-3977

**ተማሪ የቦርድ አባል**
www.montgomeryschoolsmd.org/boe/members/student.aspx

የትምህርት ቦርድ ጽ/ቤት ስልክ፡- . . . . . . . . 240-740-3030

የትምህርት ቤት አመራር እና ማሻሻያ ክፍል ዋና ኃላፊ . 240-740-3100

የልዩ አገልግሎት ድጋፍ ክፍል . . . . . . . . . 240-740-5630

ሰክሽን 504 አስተባባሪ . . . . . . . . . . . . . 240-987-8031

## የሞንትጎመሪ አስቸኳይ ላልሆኑ ጉዳዮች መገልገያዎች (ሪሶርሶች)

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ አስቸኳይ ላልሆነ ጥሪ የስልክ መስመር**
301-279-8000

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች የመረጃ መስመር**
የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ አጠቃላይ መረጃን ያነጋግሩ 311, 301-251-4850 TTY
ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪዎች ውጭ240-777-0311

## MCPS መረጃ እና የአስቸኳይ ጊዜ ማስታወቂያዎች

**በዚህ ድረ-ገጽ አማካይነት ከ MCPS ጋር ሁልጊዜ መገናኘት ይችላሉ፡-**
www.montgomeryschoolsmd.org

**አጠቃላይ ተቋሙን የሚመለከት መረጃና የአስቸኳይ ሁኔታ ማስታወቂያዎችን ለማግኘት፡-**

ትዊተር፡- MCPS on Twitter . . . . . . . www.twitter.com/mcps
ትዊተር በስፓንሽኛ፡- MCPS en Españolwww.twitter.com/mcpsespanol

MCPS ፌስቡክ፡- www.facebook.com/mcpsmd
ፌስቡክ በስፓንሽኛ፡- MCPS en Españolwww.facebook.com/mcpsespanol

**የማንቂያ/የማስጠንቀቂያ መልክቶች፡-**
Alert MCPS . . . . www.montgomeryschoolsmd.org/alertMCPS

988 SUICIDE & CRISIS LIFELINE

988 LÍNEA DE PREVENCIÓN DEL SUICIDIO Y CRISIS

## MCPS መረጃ እና የአስቸኳይ ክስተት ማስታወቂያዎች (የቀጠለ)

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ፈጣን መልክቶች፣ የኢሜይል መልክቶች እና ዘገባዎች
MCPS QuickNotes Email Messages
and Newsletter . . . . . . . . . . www.mcpsQuickNotes.org

MCPS የመረጃ አገልግሎትን ይጠይቁ፡-
ስልክ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 240-740-3000
የስፓንሽኛ አስቸኳይ የስልክ መስመር . . . . . . . . 240-740-2845
Email . . . . . . . . . . . . . . AskMCPS@mcpsmd.org

MCPS የማህበረሰብ መረጃ ቢሮ . . . . . . . . . 240-740-2837
MCPS Television www.mcpsTV.org;
ቴሌቪዥን
Comcast 34, 998; RCN 89, 1058; Verizon 36

በድምፅ የተቀረጸ የአስቸኳይ ጊዜ እና የአየር ሁኔታ መረጃ . . 301-279-3673

## MCPS ሪሶርሶች የሚገኙበት ድረ-ገጽ
www.montgomeryschoolsmd.org

ዳሰሳ ወይም ቅኝት፡-

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ት/ቤቶች የመረጃዎች ዝርዝር ማውጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች የመረጃዎች ዝርዝር ማውጫ

MCPS ስልታዊ (ስትራቴጂያዊ) እቅድ

አትሌቲክስ

Be Well 365

የትምህርት ቦርድ

ጉልበተኝነት፣ ጥቃት/ትንኮሳ፣ ዛቻ/ማስፈራራት

የአውቶቡስ መስመሮች

የልጅ ማጎሳቆል እና ቸልተኝነት

የኮሌጅ እና የሙያ ማዕከል

የግንዛቤ ትምህርት
Common Sense Education

የኮርስ ጥንቅር መግለጫ

የማህበራዊ ሚዲያዎችንና ሌሎች የዲጅታል መሳሪያዎችን ኃላፊነት በተሞላበት መንገድ መጠቀምና የኢንተርኔት ደህንነት - Cybercivility and CyberSafety

የዲፕሎማ መስፈርቶች

ወሮበሎች (ጋንግ) እና የወሮበሎች ተግባር

ውጤት አሰጣጥ እና ሪፖርት ማድረግ

## MCPS የሪሶርስ ድረ-ገጽ (የቀጠለ)
www.montgomeryschoolsmd.org

የጥላቻ ዝንባሌ

የሃይማኖት ብዝሃነትን የማክበር መመርያዎች

ስለ ተማሪ ጾታዊ ማንነት መመሪያ

LGBTQ ድረገጽ

የምሣ ምግብ ዝርዝር

የሜሪላንድ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ምዘናዎች

ፀረ-መድሎአዊነት

በኦንላይን የመመረቂያ ትምህርት

የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት

መርኆች እና ደንቦች

የስነልቦና አገልግሎቶች

የተማሪ ሠራተኛ አገልግሎቶች

የልጅ መበደል እና ቸልተኝነትን ሪፖርት ማደረግ

ፍትኃዊ ተሐድሶ

በት/ቤት የካውንስሊንግ እገልግሎቶች

የትምህርት ቤት የጤና አገልግሎቶች

የትምህርት ቤት ደህንነት

ፆታዊ ጥቃት

የማህበራዊ ሚድያ ዲጂታል ሲትዝንሽፕ
(Social Media Digital Citizenship)

ልዩ ትምህርት

ልዩ ፕሮግራሞች

ስልታዊ የእቅድ ዝግጅት

የተማሪ ስነ-ምግባር ደንብ

የተማሪ በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ መማር - eLearning

የተማሪ ግላዊነት

የተማሪ አገልግሎት ትምህርት

ራስን የመግደል ሙከራን መከላከል

የሰመር ትምህርት ቤት
Summer School

ታይትል/Title IX

# መግቢያ

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)፣ ለተማሪዎች ያለን ቁርጠኝነት በመከባበር እና በእኩልነት ባህል ላይ የተመሰረተ ነው። የሜሪላንድ ህግ፣ COMAR 13A.01.06.03 ጨምሮ፣ በፆታዊ ዝንባሌ ወይም በፆታ ማንነት ምክንያት መድልዎ ማድረግን ይከለክላል። የማህበረሰባችንን ብዝሃነትና ልዩነት የምናከብር ሲሆን እያንዳንዱ ተማሪ ከፍተኛ ደረጃ እንዲደርስ እና ስኬታማ የመሆን እድል እንዳለው/እንዳላት ማረጋገጥ አለብን። ይህ ቁርጠኝነት በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA፣ አድሎ የሌለበት፣ ፍትሃዊነት፣ እና የባህል ብቃት ውስጥ በግልጽ የተካተተ ነው፣ይሄውም ሁሉንም አካታች፣ ተቀባይነት ያለው እና ፍትሃዊ የትምህርት አካባቢን ለማበልፀግ የረጅም ጊዜ ቁርጠኝነቱን ያጠነክራል። ለ LGBTQIA+ ተማሪዎቻችን ከአድልዎ፣ ከጉልበተኝነት, እና ከትንኮሳ ነፃ የሆነ ደህንነቱ የተጠበቀ እና አመቺ ቦታ መስጠት አስፈላጊ መሆኑን እንገነዘባለን። ተማሪዎች የፆታ ማንነታቸውን በትክክል እና ያለ ፍርሃት መግለጽ መቻል አለባቸው፥ እናም የተለየ ማንነታቸውን እና የህይወት ተሞክሮቻቸውን ማንፀባረቅ እና ማክበር በሚቻልበት አካባቢ ለመማር እንደሚጠብቁ እናምናለን። እንደ ት/ቤቶች ዲስትሪክት፣ የፆታ ማንነት ጉዳዮችን እውቅና ለመስጠት እና ለማክበር፣ የተማሪዎችን ጥያቄዎች በምክንያታዊነት ለመመለስ እና የእያንዳንዱን ተማሪ ግላዊነት እና ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ ቁርጠኞች ነን።

ይህን ወሳኝ ርዕስ የሚመለከቱ የተለያዩ የቦርድ ፖሊሲዎችን፣ MCPS ደንቦችን እና አፈጻፀሞችን ለማጠናከር እና ለማብራራት፣ ይህንን አጠቃላይ መመሪያ አዘጋጅተናል። ለሰራተኞቻችን፣ ለተማሪዎቻችን፣ ለቤተሰቦቻችን እና ለማህበረሰቡ ግልጽ የሆነ መግለጫ በመስጠት እና እነዚህ መረጃዎች ሁሉ በአንድ ላይ  መገኘት አስፈላጊ ነው ብለን እናምናለን። ይህን መመሪያ በማዘጋጀት ሂደት፣ ከ MCCPTA-LGBTQIA+ ንዑስ ኮሚቴ እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በንቃት ተባብረናል፣ የእነዚህ በዋጋ ሊተመን የማይችል አስተዋፅዖአቸው ለመሠረታዊ የመማር፣ የግንኙነት፣ የመከባበር፣ የልቀት እና የፍትሃዊነት እሴቶቻችን ያለንን ቁርጠኝነት አጠናክረውታል። ለእነርሱ አጋርነት እና ትብብር ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን። ለሁሉም ተማሪዎቻችን ደህንነቱ የተጠበቀ፣ አወንታዊ እና መከባበር የሰፈነበት የመማሪያ አካባቢዎችን ለመፍጠር ያለንን ቁርጠኝነት ማሳደግ የምንቀጥለው በዚህ ትርጉም ባለው አጋርነት ነው።

MCPS ተማሪዎች ለት/ቤት በተገለፀው አኳኋን እንደየ ፆታ ማንነታቸው፣ ጾታቸውን የቀየሩ፣ ወይም ጾታቸውን ለመግለፅ የማይስማሙ ተማሪዎችን ጭምር ወጥነት ባለው መልኩ በትምህርት ቤት ህይወት ውስጥ እንዲሳተፉ ይደግፋል። MCPS የሚከተሉትን ለማድረግ ይጥራል፡-

- ጾታ የቀየሩትን እና የጾታ መለያቸውን ማረጋገጥ የማይፈልጉ ተማሪዎችን መገለል መቀነስ።
- ጾታቸውን የቀየሩትን እና ጾታቸውን የማያሳውቁ ተማሪዎችን ማህበራዊ መስተጋብር እና የአካታችነትን ባህል ማዳበር።
- ተማሪዎች የፆታ ማንነታቸውን ወይም ጾታ የመቀየር ሁኔታን የግል እና ሚስጥራዊ የማድረግ መብታቸውን ማክበር።
- የተማሪ ጾታ ማንነት እና ፆታዊ አገላለጽ ጉዳዮችን በአግባብ እና በዘለቄታ ለመፍታት እንዲያስችላቸው ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሥራ ባልደረቦች ድጋፍ መስጠት።

እነዚህ መመሪያዎች እንደሚረዳዎት ተስፋ እናደርጋለን። በዚህ መመርያ ውስጥ ስላለ ማንኛውም ነገር ጥያቄ ካለ፣ እባክዎ በቅድሚያ ከት/ቤት አስተዳዳሪዎች ጋር ተነጋገሩ። ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ የተማሪዎችን የሥነ ምግባር እና ይግባኝ ክፍል፣ የተማሪዎች ደህንነት እና የደንብ ማስከበር ቡድን በስልክ ቁጥር (240) 740-3215 ወይም SWC@mcpsmd.org ያግኙ። ስለ ተማሪ ጾታ አጠር ያለ መመሪያ አለ። ጥያቄዎችዎን የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች መመለስ የማይችሉ ከሆነ፣ የትምህርት ቦርድ ሰራተኞች ዋና ኃላፊን በስልክ ቁጥር 240-740-3030 ወይም boe@mcpsmd.org ማግኘት ይችላሉ።

## ■ ትርጉም

እዚህ ላይ የተሰጡት ትርጓሜዎች ልውጥ ጾታ እና ጾታቸውን መግለጽ ያልቻሉ ተማሪዎችን ለመደገፍ እንጂ ተማሪዎችን ለመፈረጅ ታስቦ አይደለም። ተማሪዎች እራሳቸውን ለመግለጽ እነዚህን ቃሎች ሊጠቀሙ ወይም ላይጠቀሙ ይችላሉ።[3፣4]

AGENDER (ከየትኛውም ጾታ ያልሆኑ) የጾታ መገለጫ የሌላቸው (እንዲሁም "ያለጾታ" ወይም "ጾታ የሌለው") ።

የተወለደ(ች)በት ጾታ ስያሜ/CISGENDER የጾታ ማንነት እና የጾታ አገላለጽ የተወለደ(ች)በትን የጾታ ስያሜ የያዘ/ች ሰው፣ ጾታ ያልቀየረ/ች ሰው ወይም ሥርዓተ-ፆታ የማያሟላ/የማታሟላ(የማያረጋግጥ/የማታረጋግጥ) ሰው ።

የሥርዓተ-ፆታ አገላለጽ አንድ ሰው ጾታን ለሌሎች የሚገልጽበት መንገድ፣ ብዙ ጊዜ በባህሪ፣ በአለባበስ፣ በፀጉር አሠራር፣ በእንቅስቃሴ፣ በድምጽ፣ በንግግር እና በቃላት ምርጫ ወይም በስነምግባር ይሆናል።

ጾታቸውን በመግለጽ የሚወላውሉ-GENDER FLUID የጾታ ማንነቱ(ቷ) ወይም የጾታ መገለጫ(ዋ) ቋሚ ያልሆነ እና እንደየሁኔታው የሚቀያይር-የምትቀያይር ሰው።

የሥርዓተ -ፆታ ማንነት አንድ ሰው በጥልቅ የያዘው-የያዘችው ውስጣዊ ስሜት ወይም የግለሰብ ጾታ ሥነ ልቦናዊ ዕውቀት። የአንድ ሰው የጾታ መገለጫ በትውልድ ከተሰጠው/ከተሰጣት የጾታ ማንነት ጋር አንድ ዓይነት ወይም የተለየ ሊሆን ይችላል። ብዙ ሰዎች በተወለዱ ጊዜ ከተሰየሙት የጾታ መለያ/ማንነት ጋር የሚገጣጠም የጾታ መገለጫ አላቸው። ቢሆንም እንኳ፣ ለአንዳንዶች፣ የፆታ ማንነታቸው በተወለዱበት ጊዜ ከተሰየመላቸው የፆታ መለያ የተለየ ነው። ጾታቸውን የቀየሩ ወይም ጾታቸውን የማያረጋግጡ/የማይገልጹ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ሰዎች ሁሉ የጾታ ማንነት አላቸው። ለዚህ መመሪያ ዓላማ፣ የአንድ ተማሪ ፆታው(ዋ) በት/ቤት ውስጥ በተደጋጋሚ በይፋ የታወቀ/የተረጋገጠው ነው።

GENDER NONCONFORMING/ሥርዓተ -ፆታ የማያሟሉ በማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት ካለው/ከተለመደው/ባህላዊ ከሆነው የተለየ አገላለጽ ወይም የተወሰነ ወይም "አንስታይ/FEMININE" ወንዶች፣ "ተባታይ/MASCULINE" ልጃገረዶች፣ የማይለወጥ አመለካከት የመሣሡ እና ጾታዊ አገላለጻቸው አንድሮጅነስ/ANDROGYNOUS/ከፊል ወንድ ከፊል ሴት የሆነ/ች። ይህ የሚያካትተው በተለምዶ ከሚታወቀው ዓይነት የፆታ አገላለጽ ስያሜ ውጪ ወይም እንደ ሁለት ወይም የበለጠ (የተለየ) ፆታዊ ማንነት እንዳላቸው የሚገልፁትን ነው። ሌሎች ተመሳሳይ ትርጓሜዎች ለኖራቸው የሚችሉ ቃላት የሚያካትቱት "የሥርዓተ-ፆታ ልዩነት/ልዩ ልዩ ፆታ" ወይም "ጾታን የሚያራምዱ/የሚያስፋፉ" ናቸው።

ወንዳገረድ/INTERSEX ወንድ ወይም ሴት ተብሎ ከሚገለፀው መደበኛ የጾታ አገላለጽ ጋር የማይገጥም አካላዊ ወሲባዊ/ጾታዊ ባህሪያት ከማሳደግ ጋር የተያያዙ በርካታ ሁኔታዎች።

LGBTQIA+ ሌዝቢያን፣ ጌይ/ግብረ ሰዶማዊ፣ ጣምራ ጾታ፣ የፆታ ለውጥ ያደረገ(ች)፣ QUEER/QUESTIONING፣ ኢንተርሴክስ እና አሴክሹዋልለሌዝቢያን፣ ጌይ/ግብረ ሰዶማዊ፣ ጣምራ ጾታ፣ ትራንስጀንደር/የፆታ ለውጥ ያደረገ(ች)፣ QUEER እና ስለ ጾታ ጠያቂ/QUESTIONING ማህበረሰብ ምህጻረ ቃል ነው። ይህ ምህጻረ ቃል ብዙውን ጊዜ ሁሉን አቀፍ ለመሆን ሲባል LGBTQIA+ ተብሎ ይጻፋል። እንዲሁም ግብረ-ሰዶማዊ፣ ወንዳገረድነት ወይም ከላይ የተጠቀሱትን ሁሉ የሚወክሉ ሰዎችን ለማካተት ይጻፋል።

ከሁለቱም ያልሆነ ወንድ ወይም ሴት ተደርጎ የማይለይ፣ ወይም በጭራሽ ጾታ የማይለይ ሰው። አንዳንዶች ከተለምዶ ጾታ የሚለዩ ሰዎች ጾታቸውን የቀየሩ ናቸው።

በመወለጃ ጊዜ የተሰየመ ጾታ በህፃንነት የልደት ሠርተፊኬት ላይ የተሰየመ ጾታ፣ በልደት ቀን/በተወለዱበት ቀን እንዲህ ዓይነት ሰነድ/ምዝገባ መሰጠት አለበት።

ጾታዊ መገለጫ የአንድን ሰው ስሜታዊ፣ የፍቅር ግንኙነት፣ ወይም ለሌላ ሰው የፍቅር ዝንባሌን ይገልጻል። አንዳንድ የፆታ ዝንባሌ ምሳሌዎች፦ ቀጥታ በወንድና በሴትነት የተለየ/ ሄትሮሴክሹዋል፣ ጌይ፣ ሌዝቢያን፣ የወንድም የሴትም የጾታ አካል ያለው/ያላት፣ ያለ አባለዘር/ጾታ የለሽ፣ ወይም ፓንሴክሹዋል ናቸው።

የጾታ ለውጥ የአንድ ሰው የጾታ ማንነት ወይም መገለጫ ከተለመደው በተወለደ/ች ጊዜ ከተሰየመ ጾታ የተለየ ቅጽላዊ አገላለጽ ነው። ተመሣሣይ ትርጉም የሚኖራቸው ሌሎች ቃሎች " ቅይር ሴት/ወንድ TRANSSEXUAL (ሴት ነኝ ብሎ የሚያምን ወንድ/ወንድ ነኝ ብላ የምታምን ሴት-- በቀዶ ጥገና ፆታውን ያስቀየረ/ያስቀየረች) " እና " ቅይር/TRANS "

ትራንዚሽን ሰው በተወለደ(ች)በት ጊዜ ከተሰጠው/ከተሰጣት ጾታ ይልቅ፣ ራሱ(ሷ) በሚሰይመው/በምትሰይመው ጾታ ለመኖር የሚወስንበት ሂደት ነው የፆታ ማንነታቸውን ለሌሎች ሰዎች ለመግለጽ፣ ጾታ የቀየሩ ትራንስጀንደር ሰዎች የተለያዩ እርምጃዎችን ሊወስዱ ይችላሉ (ለምሳሌ፦ ቅጽል ስም በመጠቀም ወይም በህጋዊ መንገድ ስማቸውን እና/ወይም የፆታ ስያሜያቸውን በህጋዊ ሰነዶች ላይ መቀየር፣ የፆታ ማንነታቸውን የሚያንፀባርቁ ልብሶች እና የፀጉር አበጣጠር መምረጥ እና በአጠቃላይ ከፆታ ማንነታቸው ጋር በቋሚነት ራሳቸውን ለሌሎች ይገልጻሉ። ጥቂቶች፣ ነገር ግን ሁሉም አይሆኑም፣ ፆታቸውን የሚቀይሩ ሰዎች እድገ-ንጥር/ሆርሞን/መድኃኒት ይወስዳሉ ወይም በቀዶ ጥገና ህክምና ተለውጦ ሰውነታቸው ከፆታ ማንነታቸው ጋር እንዲመሣሰል ያስደርጋሉ። ምንም እንኳን ሽግግር የአንድን ሰው የሥርዓተ -ፆታ ማንነት ሕዝባዊ አገላለጽ የሚያካትት ቢሆንም፣ ሽግግር የግል ሂደት ሲሆን ሽግግር ያላቸው ግለሰቦች የግላዊነት መብት አላቸው።

X MARKER ለወንድ "M" ወይም ለሴት "F" የሥርዓተ -ፆታ አመልካች ምድቦችን የማይለይ ሰው

## ■ ፆታ ከቀየሩ እና ፆታቸውን ከማይገልጹ ተማሪዎች ጋር በቀዳሚነት/Proactively አብሮ መሥራት

### የሥርዓተ -ፆታ ድጋፍ ዕቅድ

ርእሰመምህር (ተወካይ)፣ ከተማሪዎች እና ከወላጆቻቸው/ቤተሰቦቻቸዉ ጋር በመተባበር (ቤተሰቡ ተማሪው(ዋ)ን የሚደግፉ ከሆነ)፣ በት/ቤት ጠቅላላ ፕሮግራሞች እና እንቅስቃሴዎች ላይ በእኩል የመሣተፍ እድል እንዲኖራቸው እና በት/ቤት ጾታን መሠረት -ያደረገ አድሎአዊነት ለመከላከል የሚያስችል እቅድ/ፕላን ማዘጋጀት አለባቸው። ርዕሰ መምህር፣ ተወካይ ወይም የት/ቤት-የአእምሮ ጤና ባለሙያ (ለምሳሌ፦ የትምህርት ቤት የሥነ ልቦና ባለሙያ፣ የትምህርት ቤት ካውንስለር፣ እና/ወይም የትምህርት ቤት ማህበራዊ ሰራተኛ) መጠቀም ያለበ(ባ)ት የ MCPS ቅጽ

---

[1]ለበለጠ መረጃ እና ተጨማሪ መገልገያዎችን ዝርዝር ለማግኘት፦ "Maryland State Department of Education, Safe and Supportive Schools for All Students"ይመልከቱ። Creating Inclusive Spaces for LGBTQIA+ Students at https://marylandpublicschools.org/about/Documents/DSFSS/SSSP/SafeSpaces/LGTBQ-Guidelines-for-Gender-Identity.pdf

[2]ተዛማጅ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎች እና MCPS ደንቦች፡ ACA, ACF, JHF, JHF-RA, ACA-RA, ACF-RA, COA, COA-RA

[3] በዚህ መመሪያ ላይ የተገለጸው ሃረግ በተቻለ መጠን ሁሉን ያካተተ እንዲሆን የታሰበ ነው፣ ቢሆንም ግን፣ ሃረጎቹ እና ቋንቋ ቀስበቀስ የሚያድግ እና ቶሎ ወቅት የሚያልፍበት/የሚያረጅ እንደሆነ ግልጽ ነው።

ፍቺ/ትርጉሞቹ የተሰጡት ከዚህ ቀጥሎ ካሉት ምንጮች ነው፦ የአሜሪካ የሲቪል ነጻነት ህብረት፣ የአሜሪካ የስነ-ልቦና ባለሙያዎች ማህበር፣ የባልቲሞር ከተማ ትምህርት ቤቶች፣ የካሊፎርኒያ የትምህርት ቦርዶች ማህበር፣ የቺካጎ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች፣ ዲስትሪክት ኦቭ ኮሎምቢያ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች፣ ጌይ፣ ሌዝቢያን እና ቀጥተኛ ጾታ የትምህርት መረብ፣ ሃዋርድ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች፣ የሰብአዊ መብት ዘመቻ፣ Lambda Legal፣ የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ፣ ሜሪላንድ የሕዝብ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አትሌቲክስ ማህበር፣ የማሳቹሴትስ የአንደኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መምሪያ፣ ብሔራዊ የኮሌጆች አትሌቲክስ ማህበር፣ ብሔራዊ የትምህርት ቦርዶች ማህበር፣ የኒው ዮርክ ከተማ የትምህርት መምሪያ፣ PFLAG፣ እና ትሬቨር ፕሮጀክት።

560-80 *የመቀበያ ቅጽ፡- ለተማሪዎች የጾታ መለያ ድጋፍ መስጠት*
ይህንን ሂደት መደገፍ፣ ተማሪ በትምህርት ቤት ተሳታፊ እንዲሆን-እንድትሆን መደገፍ ነው። የተሞላው ቅጽ በተማሪ ፋይል ማጠራቀሚያ ወይም ሚስጥራዊ ፋይሎች ላይ ሳይሆን አስተማማኝ በሆነ ስፍራ መቀመጥ አለበት። እቅዱ/ፕላኑ በሁሉም የት/ቤት ባልደረቦች በትክክል/በቋሚነት የሚተገበር ቢሆንም ቅጹ ራሱ በሌሎች የት/ቤት ባልደረቦች መታየት ወይም ሊጠቀሙበት አይገባም።

- የእያንዳንዱ ተማሪ ፍላጎት እንደ ጉዳዩ ሁኔታ አንድ-በአንድ መገምገም አለበት፣ እና ሁሉም እቅድ በሂደት እየተገመገመ እንደአስፈላጊነቱ ይከለሳል። የእቅዱ አካል እንደመሆኑ፣ ትምህርት ቤቶች ከተማሪው(ዋ) ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሚኖራቸውን የሥራ ባልደረቦች መለየት አለባቸው። እንዴት ድጋፍ እንደሚሰጥ፣ እንዴትና ለማን ኢንፎርሜሽን መነገር እንዳለበት በእቅዱ ላይ መገለጽ/መታየት/መነደፍ አለበት።
- በተጨማሪ፣ እያንዳንዱ እቅድ ይፋዊ ስም፣ ተውላጠ ስሞች፣ አትሌቲክስ፣ ከቀለም ትምህርት ተጨማሪ እንቅስቃሴዎችን፣ ሎከር ክፍሎችን፣ የመጸዳጃ ክፍሎችን፣ ሠላማዊ ቦታዎችን፣ ሠላማዊ ቀጣናዎችን፣ እና ሌላ ሠላማዊ ድጋፎችን፣ እና ምረቃ የመሣሠሉ ይፋዊ ሁነቶችን እንደሚከወን መገለጽ አለበት።

### ከቤተሰብ ጋር መግባባት

ርእሰ መምህሩ ወይም የተወከለ የሥራ ባልደረባ ተማሪው(ዋ) ከቤት ምን ያህል ድጋፍ እንደሚያገኝ/እንደምታገኝ ለማወቅ ከተማሪው(ዋ) ጋር መነጋገር አለበት። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ ጾታቸውን የቀየሩ/ትራንስጀንደር እና የጾታ ስያሜን የማይከተሉ ተማሪዎች የፆታ ማንነታቸውን በግልጽ ላይገልጹ ይችላሉ። የፆታ ማንነት ጉዳዮች ውስብስብ ሊሆኑ ይችላሉ። ድጋፍ የሚያስፈልግ ከሆነ የተማሪዎች ሥነ ምግባር እና ይግባኝ ክፍል (DSCA) መጠየቅ አለበት። እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም፣ ለተማሪ ድጋፍ መስጠት ወሳኝ መሆኑን በመገንዘብ፣ ሰራተኞች ቤተሰብን ለማካተት የሚያስችል በተማሪዎች የሚመራ እቅድ ለማዘጋጀት ድጋፍ ይሰጣሉ።

## መረጃ/ኢንፎርሜሽን ይፋ ማድረግ እና ግላዊነት

- ሁሉም ተማሪዎች ስለግል ገመናቸው መብት አላቸው። ይህ የጾታ ለውጥ ያደረጉ ወይም ጾታ የማይገልጹትን ግላዊ አቋም በት/ቤት ገመና የመጠበቅ መብትን ያካትታል።
- ስለ አንድ ተማሪ የፆታ መቀየር አቋም፣ ህጋዊ ስም፣ ወይም በተወለደ(ች) ጊዜ የተሰጠ ፆታ ከህክምና ጋር የሚገናኝ ሚስጥራዊ መረጃ ሊሆን ይችላል። ይህንን መረጃ ለሌሎች ተማሪዎች ወይም ለሶስተኛ ወገን ይፋ ማድረግ የፌዴራል የቤተሰብ ትምህርት መብቶች እና የግላዊነት ህግ (FERPA) የመሳሰሉ የግላዊነት ህጎችን መጣስ ልሆን ይችላል።
- በስቴት፣ የአካባቢ፣ እና የፌደራል የግላዊ ገመና አጠባበቅ ህጎች መሠረት፣ ጾታ የቀየሩትን ጭምር የተማሪዎች የህክምና መረጃዎችን በሙሉ በሚስጥር መጠበቃቸውን ትምህርት ቤቶች ያረጋግጣሉ።
- ስለ ጾታ አቀራረብ፣ ማንነት፣ እና ብዙሃነትን/ልዩነትን አስመልክቶ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለማስተናገድ ለት/ቤት የሃኪም ምርመራ፣ ህክምና፣ እና/ወይም ሌሎች ሠነዶች አስፈላጊ ያለመሆናቸዉን እባክዎ ይገንዘቡ።
- ጾታ የቀየሩ እና ጾታቸውን ያልገለጹ ተማሪዎች ስለ ጾታ ማንነታቸው ለመወያየት እና የጾታ ምንነታቸውን በግልጽ ለማረጋገጥ እና መቼ፣ ከማን ጋር፣ እና ምን ያክል ግላዊ ገበናን መረጃ/ኢንፎርሜሽን ለመለዋወጥ የመወሰን መብት አላቸው። ተማሪዎች ሁኔታቸውን ለሠራተኞች ወይም ለሌሎች ተማሪዎች መግለጻቸው የትምህርት ቤት ሰራተኞች የተማሪው(ዋ)ን ሁኔታ ለሌሎች ሠራተኞች፣ ለተማሪዎች፣ ወይም ለሶስተኛ ወገን እንዲገልጹ መፍቀድ ማለት አይደለም፣ በሕግ ካልተጠየቀ በስተቀር ወይም ተማሪዎች እንዲህ ዓይነቱን ይፋ ማድረግ ካልፈቀዱ በስተቀር የግል ማንነታቸውን ምስጢር መጠበቅ ያስፈልጋል።

  የተማሪው(ዋ) ወላጅ/አሳዳጊ ሲጠይቁ፣ የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ተማሪያቸው ጾታው(ዋ)ን የቀየረ(ች)/ትራንስጀንደር ወይም የጾታ ስያሜን የማይከተል/የማትከተል መሆኑን መግለጹ(ጿ)ን ማሳወቅ አለባቸው። ሰራተኞች ይህንን መረጃ ከወላጆች/ከአሳዳጊዎች መደበቅ አይጠበቅባቸውም። ይሁን እንጂ፣ ሰራተኞች በተለይም ይህን ማድረግ ለተማሪው(ዋ) ከፍተኛ የጉዳት አደጋ ሊያስከትል በሚችልበት ጊዜ እንዲህ ዓይነቱን መረጃ ከመግለጻቸው በፊት ከርእሰ መምህር ጋር መማከር አለባቸው።
- ጾታ የቀየሩትን ወይም ጾታቸውን ያላረጋገጡ ተማሪዎችን በት/ቤት ድጋፍ ለመስጠት አስፈላጊ ከሚሆነው የበለጠ በርካታ ጥያቄዎችን መጠየቅ አግባብ አይደለም።

## ስሞች/ተውላጠ ስሞች

ሁሉም ተማሪዎች በመረጡት ስም እና/ወይም ተውላጠ ስም የመጠራት መብት አላቸው። የትምህርት ቤት ሠራተኞች ተማሪዎችን በትምህርት ቤት ከተገለጸው ስም እና ተውላጠ ስም ከፆታ መገለጫቸው ጋር በማስማማት መጥራት አለባቸው። ተማሪዎች በራሳቸው ተለይተው ከተመረጡ ስሞች ጋር በሚዛመዱ ስም እና ተውላጠ ስም ለመጠራት ከታች በተጠቀሰው ክፍል በተገለፀው መሰረት እንደ ቅድመ-ሁኔታ ሆኖ ቋሚ የተማሪ ሪከርዶቻቸውን መቀየር እይጠበቅባቸውም (ለምሳሌ፡- በፍርድ ቤት-የታዘዘ ስም እና/ወይም አዲስ የልደት ሰርተፍኬት)። በተቻለ መጠን እና ከእነዚህ መመሪያዎች ጋር በሚስማማ መልኩ፣ የትምህርት ቤት ሰራተኞች FERPA ድንጋጌ መሠረት የተማሪን የጾታ መቀየር/ትራንስጀንደር ሁኔታ ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ ጥረት ያደርጋሉ።

### የሰራተኞች ግንኙነት

ትምህርት ቤቶች የተማሪ ው(ዋ)ን በተወለደ(ች)በት ወቅት የተሰየመ የጾታ መለያ እና ህጋዊ ስም በትምህርት ሪኮርዶች እና ሌሎች ሠነዶች ላይ መጠቀም ህጋዊ ግዴታ እስካልሆነ ድረስ፣ ትምህርት ቤት በተማሪው(ዋ) አማካይነት የተገለጸውን ስም እና ጾታ በመማርያ ክፍል መዝገቦች (rosters)፣ በመታወቂያ መለያ፣ በማስታወቂያዎች፣ በሠርተፊኬቶች፣ በጋዜጦች፣ በመጽሔቶች፣ እና በዓመታዊ መጽሔቶች ላይ መጠቀም አለባቸው። የተዛባ ጾታዊ አገላለጽን ወይም የስም አጠራር ግድፈትን ጎጂነት ለማስወገድ፣ በተለይም ትምህርት ቤቶች ጥንቃቄ ማድረግ የሚኖርባቸው ከሁሉም ተተኪ አስተማሪዎች ጋር የሚደረግ የመረጃ ልውውጥ ከተማሪው(ዋ) የተገለጸ ስም እና ጾታ ጋር ተመሣሣይ መሆኑን በማረጋገጥ ነው።

- ትምህርት ቤቶች የተማሪን ጾታ የሚገልጹ ወይም እንደ ወንዶች/ልጃገረዶች (ተማሪዎች በማለት ፈንታ) ወይም እናት/አባት (ወላጅ/ሞግዚት በማለት ፈንታ) ስለጾታ ገላጭ በሆኑ ቃላት የፈቃድ መስጫ ወረቀቶችን እና ሌሎች የትምህርት ቤት- ቅጾችን አጠቃቀም መቀነስ ይኖርባቸዋል።
- ስለ አስንድ ሰው ተውላጠ ስሞች መጠየቅ ጾታ ለቀየሩ፣ ጾታቸውን ለማይገልጹ፣ እና ከሁለቱም ጾታ ያልሆኑትን ይበልጥ አካታች እና አመቺነት ይፈጥራል።

## ቋሚ የት/ቤት ሪከርዶች

ት/ቤቶች ለእያንዳንዱ ተማሪ ቋሚ የሆነ ፋይል/መዝገብ ሊኖራቸው ይገባል፣ ይሄም የተማሪን ፆታ እና ህጋዊ ስም ማካተት አለበት። የተማሪን ጾታ ወይም ህጋዊ ስም መቀየር የሚፈልጉ ተማሪዎች ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎች ከት/ቤት ካውንስለር ጋር መማከር አለባቸው፣ ይሄውም ባለሙያ ቅጹን በመሙላት ቤተሰብን የሚረዳበት ቅፅ 560-80፣ የመቀበያ ቅፅ፡-ነው። የተማሪ ጾታዊ ማንነትን መደገፍ፣ እና ማንኛውንም ጥያቄ ወደ DSCA ማቅረብ። የተማሪ ጾታ እና ህጋዊ ስም ላይ የሚደረጉ ለውጦች የሚታዩት በተለየ የሜሪላንድ ስቴት ትምህርት ክፍል (MSDE) መስፈርቶች ነው። ለተጨማሪ መረጃ MCPS ደንብ JOA-RA የተማሪ ሪኮርዶችይመልከቱ።

ህጋዊ ስም ላይ የሚደረግ ለውጥ፡- የተማሪ ህጋዊ ስም መለወጡን የሚገልጽ ሠነድ ሲቀርብ ይህንኑ የተማሪ ህጋዊ ስም መለወጡን ለማንፀባረቅ የተማሪ ቋሚ ሪኮርድ ይለወጣል። ከሚከተሉት ሠነዶች/ዶኩመንቶች የትኛውም የህጋዊ ስም ለውጥ ማስረጃ ይሆናል፡-

- የልደት ሠርተፊኬት
- ፓስፖርት/ቪዛ
- የሃኪም ሠርተፊኬት
- የጥምቀት ወይም የቤተክርስቲያን ሠርተፊኬት
- የሆስፒታል ሠርተፊኬት
- የወላጅ/የአሳዳጊ ቃለ መሀላ
- ሲወለድ/ስትወለድ የተመዘገበ(ች)በት
- ሌላ የልደት ሰርተፍኬት ማረጋገጫ

አንድ ተማሪ እና/ወይም የተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ እንደዚህ አይነት ሰነዶች በሌሉበት የተማሪን ቋሚ መዝገብ/ሪከርድ እንዲቀይር ከጠየቁ፣ ትምህርት ቤቱ DSCA ማነጋገር አለበት።

የፆታ ለውጥ፡-  የተማሪ ፆታ የግል-መግለጫ/መለያ ለተማሪ ቋሚ ሪከርድ በቂ ነው። MSDE በሚሰጠው መመሪያ መሰረት፣ የተማሪ ሪከርዶች ተማሪን ወንድ፣ ሴት ወይም ጾታ X ብለው ሊለዩ ይችላሉ። የሜሪላንድ የተማሪዎች መዛግብት ስርዓት መመሪያ የተማሪን ጾታ በተማሪ መዛግብት ላይ ራሱን እንዲለይ ይፈቅዳል።

1-ወንድ

2-ሴት

X-ከሁለቱም ፆታ ያልሆነ፣ ወንድ ወይም ሴት ወይም ሁለቱንም ፆታ የማይለይ ተማሪ ነው።

ይፋ ማድረግን መከላከል፡- በተማሪ ጾታ እና/ወይም ህጋዊ ስም ለውጥ ከተደረገም በኋላ ት/ቤቱ የቀድሞውን የተማሪ ማንነት መጠበቅ አለበት። ለተጨማሪ መረጃ እባክዎን የተማሪ ሪከርድ ያዥ መመሪያን፣ የጋራ ተጠያቂነት መመሪያ ወይም SWC ይመልከቱ።

ትምህርት ቤቶች ለመደበኛ ፈተናዎች ወይም ለሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት (MSDE) ሪፖርቶች ለመሳሰሉ ከተማሪ ቋሚ ሪኮርዶች ላይ የሚገኙ ጾታ እና ህጋዊ ስሞችን እንዲጠቀሙ በሚያስፈልግበት ወቅት፣ የትምህርት ቤት ሥራ ባልደረቦች እና አስተዳዳሪዎች የተማሪ ጾታን እና ህጋዊ ስምን ይፋ በማድረግ ሆን ተብሎ የሚደርስ ጉዳትን ለማስወገድ ጥንቃቄ ማድረግ ያለባቸው ከተማሪው(ዋ) መለያ ስምና ጾታ የተለየ በሚሆንበት ጊዜ ነው።

ቋሚ የት/ቤት ሪከርድ ላይ የጾታ እና/ወይም የስም ለውጥ ሲደረግ—

- ወደ MSDE ተገቢውን ሁኔታ ማሳወቅ እንዲቻል፥ ትምህርት ቤቱ ለጋራ ተጠያቂነት ዲፓርትመንት (Department of Shared Accountability) ማሳወቅ አለበት፣ እና
- የት/ቤት አስተዳደሮች ቤተሰቦች ከውጪ (ለምሳሌ፡- የክትባት ሪከርዶች፣ የዶክተር ትዕዛዞች፣ ወይም ከህክምና ሌላ ሪከርዶች) የማንኛውም ሪከርዶች ማሻሻያ የተደረገበት ግልባጭ ለት/ቤት እንዲያቀርቡ መምከር አለባቸው።

የቀድሞ ተማሪዎች፡- በተመሳሳይ መልኩ፣ የቀድሞ ተማሪ ቋሚ ሪከርድ መቀየር ያለበት የቀድሞ ተማሪ ጾታ እና/ወይም ህጋዊ ስም ላይ የተደረገ ለውጥን ለማንፀባረቅ ነው፣ ይሄም የሚሆነው ጾታ እና/ወይም ህጋዊ ስም መለወጡን የሚያሳይ ሰነድ በተቀበለ ጊዜ ነው። እነዚህ ለውጦች የሚከናወኑት በማእከላዊ ሪኮርዶች/መረጃ ነው።

## የአለባበስ ደንብ/ሥርዓት

- ጾታ የቀየሩ ወይም ጾታቸውን የማይገልጹ/የማያረጋግጡ ተማሪዎች የ MCPS የአለባበስ ኮድ ጋር እስካልተቃረነ ድረስ፣ የጾታ ማንነታቸውን  ወይም ጾታቸውን ገላጭ የሆነ አለባበስ የመልበስ መብት አላቸው። የትምህርት ቤት ሥራ ባልደረቦች ጾታ በቀየሩ ወይም ጾታቸውን ለይተው ያላሳወቁ/የማያረጋግጡ ተማሪዎች ላይ ስለ አለባበስ ኮድ በሌሎቹ ተማሪዎች ላይ ከሚያደርጉት የተለየ ጫና ማድረግ አይኖርባቸውም።
- ትምህርት ቤቶች ከሥርዓተ-ፆታ-ገለልተኛ የሆነ የአለባበስ ደንቦችን ሲያወጡ የክፍል  ወይም ዓመታዊ መጽሔት ፎቶግራፎች፣ የማኅበረሰብ ክብረበዓላት፣ የምረቃ ሥነ ሥርዓቶች እና ዳንሶችን ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው። በተጨማሪም፤ በጾታ የተለየ ልብስ በሚለበሱበት ሁኔታዎች (ለምሳሌ፡- በትእይንቶች እና ትርኢቶች ጊዜያት)፣ ተማሪዎች ከጾታ መገለጫቸው ጋር የሚስማማ ልብስ እንዲለብሱ መፈቀድ አለበት።

## በጾታ ላይ የተመሰረቱ ተግባሮች

- ት/ቤቶች በጠቅላላ በጾታ ላይ የተመሠረቱ ፖሊሲዎችን፣ ህጎችን፣ እና አፈጻጸሞችን መገምገም ይኖርባቸዋል፣ እና ከትምህርታዊ ዓላማ ጋር የሚስማሙትን ብቻ መጠበቅ አለባቸው። ለምሳሌ፡- የሙዚቃ እና የውዝዋዜ ቡድኖች ተማሪዎችን በተለያዩ ክፍሎች የሚመድቡ ከሆነ፣ በጾታ ከመከፋፈል ይልቅ በድምፅ አይነት/ጥራት ቢመድቧቸው ይሻላል።
- በትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ወይም ሌሎች ህጋዊ በሆነ ጾታ-ተኮር ህግ፣ ፖሊሲ፣ ወይም አፈጻጸሞች፣ ተማሪዎች በጾታ በሚለዩበት ማናቸውም ጊዜ ተማሪዎች ከጾታ ማንነታቸው ጋር የሚጣጣም ተሳትፎ እንዲያደርጉ መፈቀድ አለበት።

## በጾታ የተለዩ አካባቢዎች

- የመገልገያ ቦታዎች/ፋሲሊቲዎች በፆታ ተለይተው የተመደቡ ሲሆኑ፣ ለተማሪዎች በፆታ የተለዩ መገልገያዎችን (ለምሳሌ፡- መፀዳጃ ቤት፣ ዕቃ መቆለፊያ ክፍሎች፣ እና የልብስ መቀየሪያ ክፍሎች) በቋሚነት በትምህርት ቤት ከተገለጸው የፆታ ማንነታቸው ጋር በማጣጣምመመቻቸት አለባቸው።
- በደህንነት ስጋት፣ የግል ሁኔታ፣ ወይም በሌላ ምክንያት የጋራ መገልገያዎችን ለመጠቀም ምቾት ከማይሰማው-ከማይሰማት ማንኛውም ተማሪ ጥያቄ የሚቀርብ ከሆነ፣ የተናጠል መፀዳጃ ክፍል ወይም የመቆለፊያ ክፍሎች፣ በመልበሻ አካባቢዎች ተከልለው የሚጠቀሙበት መጋረጃ፣ በአቅራቢያ የሚገኝ የግል መፀዳጃ ክፍል ወይም ቢሮ መጠቀም፣ ወይም የተለያየ የመቀየሪያ ጊዜ-ሠሌዳ እንዲደረግ እና ሠላማዊ እና ሃፍረትና መሸማቀቅ በማይሰማቸው ሁኔታ መጠቀም የሚያስችላቸው አማራጭ መሰናዶ ሊደረግላቸው ይገባል።  ተማሪው/ዋ እንዲጠቀም/እንድትጠቀም መደረግ ያለበት ሚስጥራዊነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ነው።
- በፆታ አምሳያነት ካላቸው ተማሪዎች ጋር በጋራ ለመጠቀም ለሚችሉ ተማሪዎች ሌላ አማራጭ እንዲዘጋጅላቸው አያስፈልግም። አማራጭ ሁኔታ ለመጠቀም በተማሪው/ዋ ጥያቄና የጾታ ለውጥ ያደረገ/ች ተማሪን ግላዊ ሚስጥር ለመጠበቅ በሚያስችል ሁኔታ ነው።
- አንዳንድ ተማሪዎች በፆታ ተለይቶ የተመደበ መገልገያ ፆታው(ዋ)ን ከቀየረ/ች ተማሪ ጋር ለመጠቀም አይመቻቸውም ይሆናል። ይሄ ያለመመቸት ፆታው(ዋ)ን ለቀየረ/ች ተማሪ እንዳይ(ት)ጠቀምበት ለመከልከል ምክንያት ሊሆን አይችልም። ስለ ጾታ ማንነት ግንዛቤ እንዲኖር እና የሁሉንም ተማሪዎች ባህልና ወግ ማክበርን ለማዳበር ተማሪዎች ያልተመቻቸውን ሁኔታ ለማስተካከል የት/ቤት አስተዳዳሪዎች እና ካውንስል የሚያደርጉ የሥራ ባልደረቦች ከተማሪዎች ጋር መሥራት አለባቸው።

## አዲስ ግንባታ/እድሳት

- አሁን ባሉት ፋሲሊቲዎች የትምህርት ቤት አስተዳደር ለተማሪዎች የጾታ-ገለልተኛ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችላቸው ቁመና ከሌላቸው፣ ትምህርት ቤቶች አሁን የሚገኙትን ፋሲሊቲዎች በማደስ-በማሻሻል ተፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት እንዲችሉ ከ"Department of Facilities Management" ጋር መሥራት አለባቸው።
- ለተማሪዎች ሠላም/ደህንነት ግንዛቤ በመስጠት፣ የመገልገያዎች አስተዳደር ዲፓርትመንት ጾታ-ገለልተኛ የሆነ መጸዳጃ ለተማሪ/ለህዝብ መጠቀሚያ ንድፍ/ዲዛይን ማዘጋጀት አለበት።
- አስፈላጊነቱ ከታመነበት፣ MCPS በእያንዳንዱ ደረጃ-ፎቅ/ፍሎር እና ሰው በሚበዛበት አካባቢ ቢያንስ አንድ ፆታ-ገለልተኛ ሽንት ቤት መስራት አለበት።
- በተቻለ መጠን፣ MCPS ቢያንስ አንድ ጾታ-ገለልተኝነት ያለው የአልባሳት መቀየሪያ በአዲሶቹ ት/ቤቶች እና የት/ቤት እድሳት ዲዛይኖች ላይ ማካተት ያለበት ሲሆን፣ ጾታ-ገለልተኛ የሆነ መገልገያ ዲዛይን ሲዘጋጅ ለደህንነት የማያሰጋ ሠላማዊ እና ገበናን ለመጠበቅ የሚያስችል መሆኑ በዲዛይኑ እና በቦታ አመራረጡ ግንዛቤ ዉስጥ መግባት አለበት።

## የአካል እንቅስቃሴ ትምህርት እና በት/ቤቶች ውስጥ የሚካሄድ ስፖርት

- ምንጊዜም ት/ቤት በጾታ-የተለየ የአካል እንቅስቃሴ ትምህርት ሲሰጥ እና በት/ቤቶች ውስጥ ባሉ ስፖርቶች፣ ተማሪዎች ከፆታ መለያቸው ጋር በሚመጥን ስፖርት እንዲሳተፉ ሊፈቀድላቸው ይገባል።

## በት/ቤቶች መካከል የሚካሄድ አትሌቲክስ

- የሜሪላንድ ህግ፣ COMAR 13A.01.06.03 ጨምሮ፣ በፆታዊ ዝንባሌ ወይም በፆታ ማንነት ምክንያት መድልዎ ማድረግን ይከለክላል። በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውስጥ ጾታ ያስቀየሩ እና ጾታዊ ስያሜአቸውን የማያረጋግጡ  ተማሪዎች በኢንተር-ስኮላስቲክ የአትሌቲክስ ቡድኖች ውስጥ ያለ አድልዎ እኩል የመሳተፍ እድል ይፈቀድላቸዋል፡-
  - በተወለደ(ች)በት ጊዜ የተሰየመ የተማሪ ጾታ፣ ወይም
  - ተማሪው(ዋ) ለውጥ ያደረገ(ች)በት ጾታ ወይም
  - የተማሪ የፆታ ማንነት በትምህርት ቤት በቋሚነት ይገለጻል።
- አንድ ጊዜ MCPS በትምህርት ቤት ውስጥ በተከታታይ ከተገለፀው የተማሪ የፆታ ማንነት ጋር በሚዛመድ በኢንተር-ስኮላስቲክ የአትሌቲክስ ቡድን ውስጥ ለመሳተፍ ብቁ የመሆን ውሳኔ ከተደረገ (MCPS ቅጽ 560-80 ላይ እንደተገለጸው)፣ ተማሪ interscholastic አትሌቲክስ ውስጥ የመሣተፍ ብቁነቱ ይኖረዋል/ይኖራታል።
- ትምህርት ቤቶች በአትሌቲክስ ለመሳተፍ ብቁ መሆንን በተመለከተ ማንኛውንም ይግባኝ ወደ MCPS የአትሌቲክስ መምሪያ ማቅረብ አለባቸው።
- በሌሎች ት/ቤቶች የሚደረግ ውድድር፡- በተማሪ ስምምነት እና የተማሪው(ዋ) አገልግሎት አካል ተደርጎ በአካባቢ ት/ቤት የሚሰጠው አይነት መገልገያ በሌሎችም መገልገያዎች/facilities እንዲኖር መደረግ አለበት። ኮች/አሰልጣኝ ወይም ተማሪው/ዋ የሚ(ምት)ማርበት ት/ቤት በሌላኛው በሚጎበኘዉ ት/ቤት ስለ ማንኛዉ ም አስፈላጊ ነገሮች፣ የተማሪው/ዋ ማንነት በሚስጥር እንደተጠበቀ ሆኖ ማሳወቅ አለበት/አለባት።

## ክለቦች

- ብዙ የ MCPS መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የ LGBTQ ን እና የጾታ ምንነትን የማይነግሩ ተማሪዎችን፣ እንደ ጾታ እና የወሲባዊነት መጎዳኘት (GSA) ክለቦች የሚገናኙ እና የሚደግፉ በተማሪዎች የሚመሩ ክበቦች አሏቸው። እነዚህ ክለቦች እንደማናቸውም ሌሎች ክለቦች ግልጽ በሆነ ዓላማ መካሄድ አለባቸው።
- በአከራካሪ እና ውስብስብ የህግ ጉዳዮች ላይ ውይይት በማድረጋቸው ምክንያት ብቻ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎችን ቡድን ከመፍጠር ሊያግዱ አይችሉም።

## ከክፍል ውጭ ትምህርት/ምሽቱን በሙሉ የሚቆይበት የመስክ ጉዞዎች

- ተማሪዎች በትምህርት ቤት በቋሚነት በተገለጸው የፆታ ማንነታቸው መሰረት እንዲሳተፉ መፍቀድ አለባቸው።
- የመኝታ ዝግጅትን በተመለከተ (ከመማሪያ ክፍል ውጭ ለሚሰጥ ትምህርት አዋቂዎች በሚቆጣጠሩበት ነጠላ አልጋዎች) ከተማሪው(ዋ) እና ከቤተሰብ ጋር (ቤተሰቡ ተማሪው(ዋ)ን የሚደግፍ ከሆነ) መነጋገር ያስፈልጋል። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘና ጥያቄ ከቀረበ፣ ሠላምና ደህንነት የተጠበቀና ማሸሚጠዋ የሌለበት አማራጭ የግል መኝታ አካባቢ የመሳሰለ መሰናዶ መሰጠት አለበት።
- ት/ቤቶች ማናቸውንም የግል ገበና ለመጠበቅ የሚፈልግ/የምትፈልግ ተማሪ ፣ በተቻለ መጠን ፣ ከሌሎች ተማሪዎች ባለማግለል ለማስተናገድ መሞከር አለባቸው።
- የአዳር ትምህርታዊ ጉዞዎች ሲኖሩ የሆቴል አልጋ/ክፍል በጋራ የሚጠቀሙ  (ያለ አዋቂ ቁጥጥር)  የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ወላጆች የልጃቸውን ከሌላ ተማሪ ጋር አብሮ የመመደብ ሁኔታ ማሳወቅ አለባቸው። ፆታ ያስቀየሩ ትራንስጀንደር/ከሁለቱም ፆታ አይደለሁም የሚሉ ተማሪዎች ሌሎች በተወለዱበት ጊዜ ያገኙት ተመሳሳይ ባዮሎጂካዊ ጾታ ካላቸው ተማሪዎች ጋር ብቻ የሚጋሩት ክፍል አማራጭ ሊሰጣቸው ይችላል፤ ወይም ለትራንስጀንደር በተመደበ ክፍል ውስጥ የመሆን አማራጭ ሊሰጣቸው ይችላል።
- የተማሪው(ዋ) የጾታ መቀየር/ትራንስጀንደር ሁኔታ ሚስጥራዊ መረጃ ሲሆን የትምህርት ቤት ሰራተኞች የተማሪው(ዋ)ን የየጾታ መቀየር/ትራንስጀንደር ሁኔታ ለሌሎች ተማሪዎች ወይም ከመስክ ጉዞ ጋር በተያያዘ ምክንያት ለሌሎች ተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ከተማሪው(ዋ) እና/ወይም ከተማሪው(ዋ) ወላጅ/አሳዳጊ ፈቃድ ውጭ መግለጽ የለባቸውም።

## ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት እና የዛቻና ማስፈራራት ግምገማ

- LGBTQIA+ ተማሪዎች የጉልበተኝነት፣ የትንኮሳ፣ ወይም የማስፈራራት እንዲሁም የራስን ሕይወት የማጥፋት አስተሳሰብ የመከሰት እድል ከፍተኛ ነው፣ በተለይም LGBTQIA+ ካልሆኑ ተማሪዎች ጋር ሲነጻጸር ራስን የማጥፋት ሙከራ የማድረግ ዕድላቸው ከአምስት እጥፍ በላይ ነው።
- የቦርድ ፖሊሲ JHF፣ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት፣ ቦርዱ ከጉልበተኝነት፣ ከትንኮሳ፣ ወይም ከማስፈራራት ነጻ የሆነ የትምህርት አካባቢ እንደሚኖር ያለውን ቁርጠኝነት ያረጋግጣል። MCPS ደንብ JHF-RA፣የተማሪ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት፣ በትምህርት ቤቶች ውስጥ የጉልበተኝነት ክልከላን የሚመለከቱ ደንቦችን ይደነግጋል። እነዚህ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS ) ድረገጽ ላይ ይገኛሉ፡- https://www.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy/pdf/jhf.pdf and https://www.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy/pdf/jhfra.pdf.
- የቦርድ ፖሊሲ - "Board Policy COA" ስለ ተማሪ ደህንነት እና የትምህርት ቤት ሠላም - Student Well-being and School Safety ስነምግባሮችን በመመርመር እና ተገቢውን የመከላከል ወይም የእርምት እርምጃዎችን በመውሰድ ሠላማዊ የትምህርት ቤት እና የሥራ አካባቢዎችን ስለመጠበቅ የባህርይና የስነምግባር ስጋቶችን የመከታተል-የመገምገም ሂደቶችን ዘርግቷል። ሁሉም ልጆች አካላዊ፣ ማህበራዊ፣ እና ስነልቦናዊ ደህንነታቸውን የሚደግፍ ሠላማዊና የሚያበለጽግ የትምህርት ቤት ድባብ እንዲኖራቸው ይገባል። ከቦርድ ፖሊሲ ACA፣ አድልዎ የሌለበት፣ ፍትሃዊነት፣ እና ባህላዊ ብቃት ጋር በሚጣጣም መልኩ፣ የትምህርት ቤት የደህንነት እርምጃዎች በተጨባጭ ወይም በሚታዩ የግል ባህሪያት ላይ ተመስርተው ወይም በሚገመት ባህርይ ላይ በመመስረት በተማሪዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የለባቸውም። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደምብ "MCPS Regulation COA-RA"፣ አስጊ ባህርይን መገምገም - Behavior Threat Assessment ፣ ላይ እንደተደነገገው በትምህርት ቤት ደረጃ የአስጊ ባህርይ መገምገምን ተግባራዊ የማድረግ ሃላፊነት ያለባቸው ሠራተኞች ውስጣዊ መዛባትን ስለመረዳት እና የብዝሃነትን ግንዛቤ ስለማዳበር፣ እና ራስን ስለመጉዳት አስጊነት ወይም ራስን ስለመግደል ዝንባሌ እውቀት እንዲኖራቸው መሰልጠን እንዳለባቸው ተገልጿል። የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ COA፥ የተማሪ ደህንነት እና የትምህርት ቤት ሠላም/ደህንነት፣ MCPS ደንብ COA-RA፣ አስጊ የሆነ ባህሪ ግምገማMCPS በይነ መረብ ላይ ይገኛል፡- www.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy/pdf/coa.pdf እና www.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy/pdf/coara.pdf
- የቦርድ ፖሊሲ JHF፣ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት ትምህርት ቤቶች ለመማር አስተማማኝ ቦታ እንዲሆኑ ከጉልበተኝነት፣ ከትንኮሳ፣ ወይም ከማስፈራራት የጸዳ አካባቢ መሆን እንዳለባቸው  ቦርዱ ያለውን ቁርጠኝነት ያሳያል። ቦርዱ የቃል፣ የአካል፣ ወይም የጽሑፍ (ኤሌክትሮኒክስን ጨምሮ) ጉልበተኝነትን ይከለክላል፣ ይህም የሳይበር ጥቃትን፣ ትንኮሳን (የጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ)፣ ማዋከብን፣ ማስፈራራትን፣ ወይም MCPS ንብረት ላይ ያለ ማንኛውንም ሰው የጥላቻ እና አድሎአዊ ድርጊቶችን ያጠቃልላል፣ ይህም ትምህርት ቤቶችን፣ MCPS በባለቤትነት የሚያስተዳድራቸው ግቢዎችን፣ MCPS አውቶቡሶችን፣ ተማሪዎችን የሚያካትቱ MCPS ስፖንሰር የሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎችን፣ ተቋም፣ ወይም ቅጥር ግቢዎችን፤ ወይም የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን በመጠቀም የሚፈፀሙ ጥቃቶችን ያካትታል።
- ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ፣ እና ማስፈራራት (እና የጥላቻ አድልዎ ክስተቶች) በተማሪው(ዋ) ትክክለኛ ወይም በሚገመት የፆታ ማንነት ወይም አገላለጽ ላይ ተመስርቶ በተማሪ ላይ የሚያነጣጠር ድርጊትን ያጠቃልላል፣ እንዲሁም ተማሪው(ዋ) ከጓደኛ፣ ከቤተሰብ አባል ወይም ከሌሎች ሰዎች ወይም ቡድኖች ጋር በሚገናኝ ባህሪ ምክንያት ተማሪን ኢላማ ያደረገ ድርጊትን ጭምር ያካትታል።
- ቋንቋን እና/ወይም ጥላቻን የሚያራምዱ ምስሎች እና ምልክቶችን ማሳየት፤ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም የማስፈራራት ሁኔታ ሊሆን ይችላል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው።
- በተማሪ ነባራዊ ሁኔታ ወይም በሚታሰበው የፆታ ማንነት ወይም አገላለጽ ምክንያት ተማሪ ላይ ያነጣጠረ ማግለል/አድሏዊነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራትን በሚመለከት የሚቀርብ ቅሬታ እንደሌሎቹ የአድሎአዊነት እና የትንኮሳ ቅሬታዎች ከሚስተናገዱበት ተመሳሳይ በሆነ መንገድ እርምጃ መወሰድ አለበት። MCPS ደንብ JHF-RA እንደአስፈላጊነቱ የተማሪ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ እና ማስፈራራት፣ MCPS ቅጽ 230-35 እና እንዲሁም MCPS ጠንካራ የተማሪ የአእምሮ ጤንነት እና ደህንነት ማመልከቻ የሪፖርት አቀራረብ ማእቀፍ ተዘጋጅቷል።  ት/ቤቶች ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ እና ማስፈራራትን በተመለከተ በንቃት መጠበቅ እና ወዲያውኑ መፍትሄ መስጠት አለባቸው።
- ጾታቸውን ስለቀየሩ ተማሪዎች እና ጾታ አስረግጠው ስለማይናገሩ ተማሪዎች በት/ቤታቸው ደህንነታቸውን ለማረጋገጥ  እና  ተማሪዎች ጾታቸውን የመግለጽ  ድፍረት እንዲያገኙ  የት/ቤት ሠራተኞች ተገቢ/ምክንያታዊ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው።
- ተማሪዎች ስለ እርግጠኛ የጾታ ማንነት ወይም ስለ ጾታ ዝንባሌ አገላለጻቸው ምክንያት የዲስፕሊን እርምጃ አይወሰድባቸውም።
- ትምህርት ቤቶች ለሁሉም ተማሪዎች LGBTQIA+ ተማሪዎች ላይ ትኩረት ያደረገ ጉልበተኝነትን ስለ መከላከል እና ችግሮችን ስለመፍታት ፕሮግራሞችን እንዲያዘጋጁ እና እንዲመሩ ይበረታታሉ።

## ሰላማዊ ስፍራዎች

- መተላለፊያ/ኮሪዶር ወይም "ውልብ" ብሎ የሚታለፍበት አስፈላጊ ከሆነ፣ ትምህርት ቤቶች ጾታ የቀየሩ ወይም ጾታቸውን ይፋ የማያደርጉ ተማሪዎች በማናቸውም ተማሪዎች ስጋት ሲኖርባቸው ወይም ምቾት በማይሰማቸው ጊዜ ሰላማዊ ወደ ሆነ ቦታ እንዲሄዱ (ለምሳሌ፡- ዋና ቢሮ፣ የካውንስለር ቢሮ) ይፈቅዱላቸዋል።
- ሰላማዊ ክልሎች፡- ትምህርት ቤቶች የአንዳንድ መምህራንን ማስተማሪያ ክፍሎች፣ የተለዩ ቢሮዎችን፣ ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ ማንኛውም ተማሪ በማንኛውም ምክንያት ከፍረጃ ነፃ እና ምቹና ከስጋት ነፃ የሚኮንበት ስፍራ/አካባቢ ይመድባሉ። በመዝጊያዎቻቸው ላይ "safe zone stickers" ያሏቸው የት/ቤት ሠራተኞች ሁሉን ያካተተ፣ የሚያረጋግጥ አካባቢ ስለማቅረብ አግባብነት ያለው ስልጠና ማግኘታቸውን ት/ቤቶች ማረጋገጥ አለባቸው።

## የሰራተኞች ድጋፍ

- የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Board of Education Policy ACA"፣ አድሎ የሌለበት፣ ፍትኃዊ፣ እና ባህላዊ ብቃት - Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency የ MCPS ሠራተኞችን በጠቅላላ ከማናቸውም አይነት አድሎ፣ ግለሰቦችን በትክክለኛ ወይም በሚገመት-ነው ተብሎ በሚታሰብ ባህርያቸው ምክንያት እና በጥላቻ ድርጊት፣ ጠብ፣ ጭቅጭቅና ረብሻ፣ ይልኙታቢስነት፣ ክብር መንሣት፣ ወይም የቃል ስድብ፣ ዛቻና ማስፈራራት፣ አካላዊ ድብድብና ግጭት፣ ዝርፊያ፣ ወይም ንብረት ማበላሸት ከመሣሰሉት ብቀላዎች፣ — ትምህርትን ወይም የሥራ አካባቢን የሚያደናቅፍ፣ እና ዘረኝነትን፣ ወንድና ሴትን እኩል አለማየትን፣ እና ጾታን የሚመለከቱ ጉዳዮችን፣ እና ሌሎች ተቋማዊ አገላለጽ ያላቸውን ፍትኃዊ ያልሆኑ ድርጊቶችን በሙሉ ይከለክላል። የሥርዓተ-ፆታ ማንነት ጉዳዮችን የሚያካትቱ መመሪያዎችን እና ድጋፎችን የሚሹ ሰራተኞች በሰው ሃብት ልማት ቢሮ፣ የቅደም ተከተል እና የምርመራ ክፍል ውስጥ ያለውን አስተባባሪ በስልክ ቁጥር 240-740-2888 እንዲያነጋግሩ ይበረታታሉ።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል" ። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

በሜሪላንድ ስቴት የሚገኙ የህዝብ ትምህርት ቤቶች እና የህዝብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ት/ቤቶች በሙሉ የሚከተሉትን ህጎች በማክበር እንዲሠሩ የስቴቱ ፖሊሲ/ድንጋጌ ነው:-

(1)የፌደራል ታይትል VI የዜኘት መብቶች ደንብ 1964፣ እና

(2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች:-

(a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፤

(b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም

(c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

የግንኙነት መርጃዎች እና የፌደራል፣ የስቴት፣ ወይ የአካባቢ መስፈርቶች በተለያዩ ሕትመቶች መካከል ልዩነት ሊኖራቸው ስለሚችል በዚህኛው ህትመት ላይ የተካተተው የሚፀና መሆኑን ልብ ይበሉ። ወቅታዊ መረጃዎችን ለማግኘት እባክዎን ይህን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination.

| MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*** | MCPS ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ *** |
|---|---|
| Department of Student Conduct and Appeals የተማሪ ስነ-ምግባር እና ይግባኝ ክፍል<br>የተማሪዎች ደህንነት እና ደንብ የማክበር ቡድን Student Welfare and Compliance Team<br>Division of Equity and Organizational Development<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ |
| Section 504 Coordinator ሰክሽን 504 አስተባባሪ<br>Division of Specialized Support Services, Department of School Counseling<br>850 Hungerford Drive, Room 170, Rockville, MD 20850<br>240-987-8031 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |

| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*** |
|---|
| Department of Student Conduct and Appeals, Title IX Team የተማሪዎች ሥነ ምግባር እና ይግባኝ ክፍል፣ ታይትል IX ቡድን<br>Division of Equity and Organizational Development<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org |

*ይህ ማሳወቂያ የተሻሻለውን የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተሟለጠ ነው።

**ይህ ማሳወቂያ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር ይሟለጣል።

***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡- U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), 61 Forsyth St. S.W., Suite 19T10, Atlanta, GA 30303, 404-974-9406 and TDD: 800-877-8339, OCR.Atlanta@ed.gov, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ"Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ሕትመት፡- Division of Communications for the Department of Student Conduct and Appeals
1101.26 • Editorial, Graphics & Publishing Services • 9/25 Amended 4/26 • NP
የቅጂ መብት፡- Copyright © 2026 Montgomery County Public Schools, Rockville, Maryland